# ኢትዮጲያዊነት ያገናኝናል

*መጋቢት 1999*

ኢትዮጵያዊያን በተለያየ ሁኔታ የተጋጩባቸው አጋጣሚዎች ቢኖሩም አጠቃላይ ኢትዮጵያን የሚመለከት ችግር ሲያጋጥማቸው የግል ቅራኔያቸውን በመተው አንድ ላይ በመሰለፍ በጋራ መዋደቃቸውን ታሪክ በተደጋጋሚ አረጋግጦታል። በቅርቡ እንኳን ኤርትራዊያን ተገንጥለናል ብለው በወያኔ ግምባር ቀደም አጋፋሪነት ነጻነታቸውን ከአወጁ በኋላ በድንበር ግጭት ተሳቦ (እኔ እንኳን መሰረታዊ መንስኢው የተባለው የድንበር ጉዳይ መሆኑን አላምንም) ከ1999-2000 እ.አ.አ በተካሂደው ጦርነት ከሁሉም ክልሎች ህዝቡ በአንድነትና በፍላጎት ላይ ተመስርቶ መዝመቱ ኢትዮጵያዊነት ምን ያህል ከሁሉም የላቀ ጉዳይ መሆኑን አረጋግጧል። ወያኔ ሲደክምለት የነበረውን በዘረኝነት በሽታ የመከፋፈል ሴራ እርቃኑን አስቀርቶታል። በወቅቱም በህዝቡ ሁኔታ አስገዳጅነት ካንገት በላይ ቢሆንም ወያኒዎችም ስለኢትዮጵያዊነት እንዲዘምሩና እንዲሰብኩ አድርጓቸው ነበር። በእውነቱ ወያኔን የለከፈው በዘረኝነት የመከፋፈል በሽታ ከህልውናው ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ዛሬም ቢሆን ከሁኒታው ሊማር አልቻለም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር ከምንም ነገር በላይ የመልካም አስተዳደር፣ የፍትህና የዲሞክራሲ… መሆኑ በይበልጥ የተረጋገጠው በምርጫ 97 ወቅት ያኢትዮጲያ ህዝብ በሁሉም ክልሎች ለቅንጅት ድምጹን መስጠቱ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጅትን ሲመርጥ ከዘረኝነት አስተሳሰብ አልፎ በመሄድ የቅንጅት ስልጣን ላይ መምጣት በእውቀት ላይ የተመሰረተ አመራር እንዲኖር ያደርጋል፣ ግልጽነት ያለው መልካም አስተዳደር ይሰፍናል፣ የባለስልጣን ጣልቃገብነት የሌለበት በህግ ላይ የተመሰረተ ፍትህ ይገኛል፣ በአገሪቱ እውነተኛ ዲሞክራሲ ይሰፍናል በማለት ነበር። ይህም ተግባራዊ ከሆነ፤ የከተማው ነዋሪ ከስራአጥነትና ከረሀብ እገላገላለሁ፤ ገበሬውም ከአካባቢው ዘራፊ ካድሬዎች ተላቅቄ፣ የመሬቱም ይዞታ ከካድሬ ባለቤትነት ወጥቶ የግሌ ስለሚሆን ሳልሸማቀቅ፣ በየጊዜው ለካድሪ ከማጐብደድና ጉቦ ከመክፈል እድናለሁ፣ እንደልቤም እሰራለሁ፤ ነጋዴውም በመንግስት የሚደገፉ የኮንትሮባንድ ነጋዴዎች ከሚያደርሱበት ተጽዕኖ ለመገላገልና አለአግባብ ከሚጣልበት ታክስ ተላቅቄ በህጋዊ መንገድ ሰርቼ ለመኖር እችላለሁ ብሎ በማሰብ ነበር። ይህም ከሆነ ኢኮኖሚው ያድጋል፣ ኢኮኖሚውም ከአደገ በአለም ላይ የረሀብና የልመና ምሳሌ ከመሆን እንድናለን በማለት ከቅንጅት ፓርቲ የተገባለትን ቃልኪዳን ተማምኖ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጅትን የመረጠው። ወያኔ እንደሚደክምለት ዘር አሽትቶ አጥንት ቆጥሮ አይደለም።

ወያኔ ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ በበተነው የዘረኛነት በሽታ የተፈጠሩ መለስተኛ ችግሮች ቢኖሩም ቀደም ሲል ለማደራጀትና አሁንም በምርጫ 97 ወቅት ለቅስቀሳ በተዘዋወርኩባቸው በአማራው፣ በኦሮሞው፣ በደቡብ፣ በአፋርና በምስራቅ የሀገሪቱ ክልሎች እንዳየሁትና ከገበሬውም ጋር ባድረግሁት ውይይት የታዘብኩት መሰረታዊው የኢትዮጵያዊነት እሴትና ወገናዊ ፍቅር እንዳለ ነው። በእርግጥ ወያኔን ከተገላገልን በኋላ መጠነኛ ስራ የሚያስፈልግ ቢሆንም ዋናው ትኩረታችን የሚሆነው ድህነታችንን ለማስወገድ ተቃቅፈን እየተረዳዳን መስራት መጀመር ይሆናል። የቅንጅት ምኞትም ይኸው ነውና።

መለስተኛ ችግሮቻችንን ለመፍታትና ተቃቅፈን ለስራ ለመነሳት ግልጽ የሆነ እውነተኛ የዲሞክራሲ ስርአት መገንባት አማራጭ የለውም። የዚህ ስርአት መገለጫው ደግሞ ማንኛውም ግለሰብ፣ ዜጋም ሆነ ድርጅት ያለምንም ስጋት የመሰለውን አመለካከት በነጻነት ማራመድና በመጨረሻም በአብዛኛው ህዝብ ፍላጎትና ድምዕ መገዛት መቻል ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የሚታሰርም ፣ የሚሰደድም፣ የሚሸፍትም አይኖርም ማለት ነው። ይህ እንዲሆን ለማድረግ የዚህ ስርአት ጠላት

ከሆነው ከዘረኝንነትና ከአምባገነንነት ጋር መታገል ያስፈልጋል። ለመታገልና የጋራ ቤታችንን ኢትዮጲያን ለማዳን የተለያየ አመለካከታችንና እምነታችን እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ መተባበርና አብሮ መስራት አስፈላጊ ይሆናል። አንዱ ለሌላው ሌላው ለአንዱ ወገናዊ ፍቅር ማሳየት ያስፈልጋል። ምርጫ 97 በኢትዮጵያ ውስጥ ያሳየንና ያስተማረንም ይህንኑ ነው። በሀገር ቤት ያለው ሁኔታ፣ በገዢው ፓርቲ የጥቅም ተካፋዮች አካባቢ ያለውን ወደ ጎን ትተንን በሌላው ህዝብ አካባቢ የሚታየው በሙሉ አበረታች ለመሆኑ ህያው ምስክር ነኝ።

በውጪ በስደት የሚኖረውስ ኢትዮጵያዊ የጋራ ቤቱን ዞሮ መግቢያውን ለማዳንና በስደት አብሮት ከሚኖረው ወገኑ ጋር ያለው ግንኙነትና መግባባት ምን ይመስላል? በእኔ በኩል የስደትን ኑሮ ከጀመርኩ ጥቂት ወራቶች በመሆኑ ምስክርነትና አስተያየት ለመስጠት አልችልም። ይሁን እንጂ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች እንደሰማሁት ከምርጫ 97 ወዲህ የታየው መቀራረብና አብሮ የመስራት አዝማሚያ አበረታች ነው። ወደፊትም መቀጠል ይኖርበታል። በውጭ ከየትኛውም ዜጋ ጋር አብረን ብንኖር ኢትዮጵያዊ ማንነታችን የማይጠፋ፣ በየትኛውም አገር ብንቆይ መሰረታችን የማይቀየር በመሆኑ ምንም አይነት የተለያየ አመለካከትና እምነት ቢኖረንም ሁላችንንም አንድ የሚያደርገን ኢትዮጵያዊነትና የጋራ ቤት አንድ አገር አለን። በኢትዮጵያዊነት ማንነታችን አንዱ ለሌላው፣ ሌላው ላንዱ ወገናዊ ፍቅር ማሳየት ቅድሚያ የሚኖረው ይመስለኛል። አብሮ በመኖር የሚፈጠሩ ችግሮችን ተገናኝቶ በመወያየት መፍታትና ግልጽነትን ማዳበር ከዚህ አልፎ የሄደ ከሆነ የሽምግልናን አስፈላጊነት ተረድቶ ያስታራቂ ሽማግሌ ኮሚቴ በማቋቋም መሸምገልና ይቅር ተባባይነትን ማዳበር ጠቃሚ ነው።

ለስደተኛው ይጠቅማሉ ተብለው የሚቋቋሙ ማህበሮችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች የድጋፍ አካለት የዲሞክራሲያዊ አሰራር መሰረቶች በመሆናቸው የመወያያና የመከራከሪያ መድረኮች እንዲሆኑ ማስቻል፤ በአመራር ላይ የሚወጡትንም ጥሩም ሰሩ መጥፎ በተወሰነ የጊዚ ገደብ በግልጽ ምርጫ እንዲቀየሩና አብዛኛው አባል በአመራር ውስጥ እንዲሳተፍ ማድረግ ተገቢ ነው። በእርግጥ አንዳንድ አመራር ላይ የነበሩ ግለሰቦች ደግመው የመመረጥ እድል ሊያገኙ ይችላሉ። ይህም ቢሆን ግልጽና ዴሞክራሲያዊ መሆን ይገባዋል።

አላማዬ ይህንን አሰራር ለስደተኛው ለማስተማር ሳይሆን እስከአሁን የሰማሁዋቸውና ያየኋቸው ሁኔታዎች በአብዛኛው አሳሳቢ መሆናቸውን ለመጠቆም ነው;; ብዙ አባል የአመራር ልምድ ማዳበሩና መምራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወቁ ተሳስቦ በጋራ ለመስራትም ጠቃሚነት ይኖረዋል ከሚል አስተሳሰብ በመነሳት ነው። አጥፍቼም ከሆነ በቅድሚያ ይቅርታ እጠይቃለሁ;; አንዳንድ የማነሳቸውና የአነሳሁዋቸው የጥቆማ ሀሳቦች የዳበረ የዲሞክራሲ ስርአቶች በሚካሄዱበት አገር የምትኖሩ በመሆናችሁ አታውቁትም ለማለት ደፍሬ አይደለም። እንዲያውም አብዛኛዎቻችሁ የማስተማር ብቃቱ እንዳላችሁ አምናለሁ። በንድፈ ሀሳብ የምናስተምረውና በተግባር የምናሳየው የተለያየ በመሆኑ ተቸግሬ ነው።

የተለያየ አመለካከት በግለሰቦችም ሆነ በድርጅቶች መካከል መከሰት ይችላል። ማንኛውም አመለካከት በግልጽ መድረክ ላይ ወጥቶ ውይይትና ክርክር በሚካሄድበት ጊዜ ግንኙነታችን ከቀረበው ሀሳብ ጋር ብቻ መሆን ይኖርበታል። ሀሳብ አቅራቢውም የቀረበው ሀሳብ እዲጸድቅለት፣ ተቃዋሚውም የቀረበውን ሀሳብ ለማፍረስ፣ አማራጭ ሀሳብ ያለውም እንዲያዝለት ለማድረግ እንጂ በተከራካሪዎች መካከል የጥላቻ መንፈስ እንዲሰርጽ ሊያደርግ ከሚችል አቀራረብ መጠንቀቅ ጠቃሚ ነው። በወቅቱ በአብላጫው ወገን ተቀባይነት ያገኘው ሀሳብ ስራ ላይ እንዲውል በወቅቱ ተቀባይነት ያጣው ሀሳብ አቅራቢዎች ቀና ትብብር ማሳየትና ለብዙሀኑ መገዛት ተገቢ ነው። ሁሉም ወገን እደግፈዋለሁ እታገልለታለሁ የሚለው ( አምባገነኖችም ሳይቀሩ) ዲሞክራሲያዊ አሰራርም

ይኸዉ ይመስለኛል። በአንድ መድረክ ላይ ተገናኝተን የምንወያየዉ የአንድ አገር ልጆች ወንድማማቾችና እህትማማቾች መሆናችንን ለአንድ አፍታም ቢሆን መዘንጋት አይገባንም።

አገራችን ኢትዮጵያ አፍሪካዊያን ከቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ ያበረከተችዉ ታላቅ አስተዋፅኦ እየተዘነጋ፣ ገናና ታሪኳ እየጠፋ፣ የዳቦ ቅርጫት እንዳልተባለች፤ ዛሬ የችጋርና የልመና ተምሳሊት በመሆን ኢትዮጵያ የአፍሪካ ማፈሪያ ተብላ በአንድ የአፍሪካ ዐሐፊ እስከመሰደብ ደርሳለች። አሁን ወያኔ በያዘዉ ሁኒታ ከቀጠለና እኛም ተባብረን አንድ ላይ በመታገል እድሚዉን ካላሳጠርነዉ ኢትዮጵያ እንደሐገር ሆና ለመቀጠል ያላት ተስፋ አጠራጣሪ ነዉ። ዛሬ ግለሰቦችን ቡድኖችን የፖለቲካ ድርጅቶችን ሊያሳስብ የሚገባው ታለቅ ጉዳይ የሃገራችን ህልውና ጉዳይ ነው። የግልም ሆነ የድርጅትን ሀሳብ መድረክ ላይ አቅርቦ ለመከራከርና ስራ ላይ እንዲዉል ጥረት ለማድረግ የሚቻለዉ ሀሳቡ የሚቀርብበት መድረክ አገርና ሕዝብ ሲኖር ነዉ። የተለያየ ሀሳብ የምናፈልቀዉ ለወገናችንና ለሀገራችን እድገት ይበጃል ብለን አስበንና ተጨንቀን ከሆነ መጀመሪያ እናስብለታለን ለምንለዉ ወገናችን እዉነተኛ ፍቅር ልንለግሰዉ ይገባል። ይህ ደግሞ እዚሁ በስደት ላይ አጠገባችን ላለዉ ወገናችን በምናሳየዉ ተጨባጭ ተግባር መፈተን አለበት። ከምንም በላይ ለኢትዮጵያዊነታችን ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል። ይህ ካልሆነ የምናልመዉ ሁሉ ባዶ ህልም ይሆናልና።

ብርቃየሁ መቀጫ 1999

ስለ ጸሃፊው

አቶ ብርቃየሁ መቀጫ በምርጫ 97 ወቅት ቅንጅትን ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ ያደረገወን የምርጫ ዘመቻ በአስተባባሪነት የመሩ፤ በሃገር ውስጥ በህዘቡና በፖለቲካ ድርጅቶች አካባቢ ስላለው ሁኔታ ሰፊና ጥልቅ እውቀት ያላቸው የቅንጅት አባል ናቸው። ቅንጅት ለምርጫ ዘመቻው እንዲመቸው ሃገሪቱን በአምስት ቀጠና ከፋፍሎ፣ ለአምስቱ ቀጠና የዴስክ ተጠሪዎች መድቦ በተንቀሳቀሰበት ወቅት አቶ ብርቃየሁ መቀጫ የአምስቱም ቀጠናዎችና ዴስኮች አስተባባሪ በመሆን ግዴታቸውን ተወጥተዋል። ይህንን በሚገባ ጠንቅቆ የሚያውቀው የወያኔ አምባገነን መንግስት አቶ ብርቃየሁን ሰኔ 1997 በመያዝ ከበርካታ የቅንጀት ደጋፊዎች ጋር በዝዋይ ማጎሪያ ጣቢያ እንዲሰቃዩ አድርጓል። እንደገናም መስከረም 16/ 1998 ከሊሊቱ 7 ሰአት የወያኔ የደህንነት አባላት አጥር ዘለዉ ከአቶ ብርቃየሁ ቤት በመግባት ዉሻቸውን ገድለው እርሳቸውንም ክፉኛ በመደብደብ ጎድናቸውን ሰብረዉ በድጋሚ ለሰባት ቀናት አስረው በዋስ ለቀዋቸዋል። አቶ ብርቃየሁ በጥቅምቱ 1998 የወያኔ እመቃ ወቅት ዳግም ለስቃይ በመፈለጋቸው ያለፍላጎታቸው ሃገራቸውን ጥለው ወደ ጎረቤት ሃገር በመሰደድ ዛሬ በአውሮፓ ውስጥ ይገኛሉ። ባቀረቡልን ጽሁፍ ላይ አስተያየት ያለው ማንኛውም ግለሰብ በኢሜል አድራሻ <simetesha@yahoo.com> ቢልክላቸው ይደርሳቸዋል።

Kinijitethiopia.org